የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17[th] Year No. 28
ADDIS ABABA 25[th] March 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፬/፪ሺ፫
የምግብ ጨው አዮዲን እንዲኖረው ለማድረግ የወጣ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..................ገፅ ፭ሺ፯፻፹፭

CONTENTS

Regulation No. 204/2011
Salt Iodization Council of Ministers Regulation ..............
............ Page 5785

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፬/፪ሺ፫

## የምግብ ጨው አዮዲን እንዲኖረው ለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፩/፪ሺ፩ አንቀጽ ፱(፬) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የምግብ ጨው አዮዲን እንዲኖረው ለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፬/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "አዮዲን ያለው ጨው" ማለት ለሰው ምግብነት አገልግሎት እንዲሆን አግባብ ባለው አካል በሚወሰነው መመዘኛ መሠረት ጨው ከአዮዲን በመደባለት የተዘጋጀ ጨው ነው፤

፪/ "አዮዲን የሌለው ጨው" ማለት ለሰው ምግብ አገልግሎት የማይውሉ ምርቶችን ለማዘጋጀት ወይም ለማምረት የሚያገለግል ጨው ነው፤

፫/ "አዋጅ" ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፩/፪ሺ፩ ነው፤

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 204/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR SALT IODIZATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 9(4) of the Food, Medicine and Health Care Administration and Control Proclamation No. 661/2009.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Salt Iodization Council of Ministers Regulation No. 204/2011".

### 2. Definitions

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "iodized salt" means salt intended for human consumption into which iodine is mixed in accordance with the specification prescribed by the appropriate authority;

2/ "non-iodized salt" means salt used in the treatment or manufacture of non-food products;

3/ "Proclamation" means the Food, Medicine and Health Care Administration and Control Proclamation No. 661/2009;

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፬/ "ማሸጊያ" እና "ገላጭ ጽሑፍ" በአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳፩) እና (፳፪) የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፤

፭/ "ተቆጣጣሪ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመደበ ተቆጣጣሪ ነው፤

፮/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ነው፤

፯/ "አግባብ ያለው አካል" ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ነው፤

፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፱/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በማናቸውም ሁኔታ ለሰው ምግብነት አገልግሎት በሚውል ጨው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ፬. ለምግብነት የሚውል ጨው አዮዲን እንዲኖረው ስለማስፈለጉ

ማንኛውም ሰው አዮዲን የሌለው ጨው ለሰው ምግብነት አገልግሎት እንዲውል ማዘጋጀት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ ማጓጓዝ ወይም መሸጥ አይችልም።

## ፭. አዮዲን ያለው ጨው ደረጃ

፩/ ማንኛውም ለሰው ምግብነት የሚውል አዮዲን ያለው ጨው አግባብ ባለው አካል በሚያወጣው የጨው ደረጃዎች መሰረት የጥራት ደረጃና መመዘኛ ማሟላት አለበት።

፪/ ማንኛውም ለሰው ምግብነት የሚውል ጨው ወደ ሃገር ውስጥ በሚገባበት ጊዜ የጤናማነት ምስክር ወረቀት ማምጣት ይኖርበታል።

## ፮. አዮዲን ያለው ጨው አስተሻሸግና ገላጭ ጽሑፍ

፩/ አዮዲን ያለው ጨው ማሸጊያ በጨው ውስጥ ያለው አዮዲን ሳይባክን እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስችል የጥራት ደረጃ ያለው መሆን አለበት።

፪/ ማንኛውም አዮዲን ያለው ጨው የሚከተሉት ገላጭ ጽሑፎች በእሽጉ ላይ በግልጽ ሰፍረው ሊታዩበት ይገባል፦

ሀ) የታሸገው ጨው አዮዲን ያለው መሆኑን፤

ለ) የአዘጋጁን ስምና ሙሉ አድራሻ፤

ሐ) የጨውን የተጣራ ክብደት፤

መ) ጨዉ የተዘጋጀበትና የአገልግሎት ጊዜው የሚያበቃበትን ወርና ዓመተ ምህረት፤



4/ "packing material" and "label" shall have the meanings assigned to them under sub-article (21) and (22) of Article 2 of the Proclamation;

5/ "inspector" means an inspector appointed pursuant to sub-article (1) of Article 5 of the Proclamation;

6/ "Authority" means the Ethiopian Food, Medicine and Health Care Administration and Control Authority;

7/ "appropriate authority" means the government organ empowered to develop Ethiopian standards;

8/ "person" means natural or juridical person;

9/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

This Regulation shall be applicable on all salts used for human consumption.

## 4. Requirement for Salt Iodization

No person shall process, import, store, transport, distribute or sale non iodized salt for human consumption.

## 5. Standard of Iodized Salt

1/ Any iodized salt for human consumption shall conform with the standards for iodized salt set by the appropriate authority.

2/ Any imported salt for human consumption shall be accompanied by a certificate of safety.

## 6. Packing and Labeling of Iodized Salt

1/ Any packing material of iodized salt shall be of such quality to preserve the iodine in the salt.

2/ Any iodized salt shall be labeled with the following information on the package:

a) the fact that the salt in the package is iodized;

b) the name and complete address of the processor;

c) the net weight of the iodized salt;

d) the month and year in which the iodized salt is processed and expired;

ሠ) የእሽጉን የመለያ ቁጥር፤ እና

ረ) ጨው በቀዝቃዛ፣ ንጹህና ደረቅ ሥፍራ ላይ መከማቸት ያለበት መሆኑን።

__ስለቁጥጥር__

፩/ ማንኛውም ተቆጣጣሪ በማንኛውም የጨው ማዘጋጃ፣ ማከማቻ፣ ማጓጓዣ ወይም መሸጫ ቦታ በመገኘት ለሰው ምግብነት የሚውል ጨው አዮዲን ያለበት መሆኑን ለመመርመርና ለማረጋገጥ ይችላል።

፪/ ተቆጣጣሪው ተግባሩን በሚያከናውንበት ወቅት በአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

__አዮዲን ስለሌለው ጨው__

አዮዲን የሌለው ጨው ለኢንዱስትሪ አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ ስለሚዘጋጅበት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገባበት፣ ስለሚከማችበት፣ ስለሚከፋፈልበት፣ ለሽያጭና ለአገልግሎት ስለሚውልበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመምከር መመሪያ ሊያወጣና አፈጻጸሙን ለመከታተል ይችላል።

__የመተባበር ግዴታ__

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ አፈፃፀም አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

__መመሪያ የማውጣት ሥልጣን__

ባለሥልጣኑ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

__ቅጣት__

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ወይም ደንቡን ለማስፈፀም የወጡትን መመሪያዎች ተላልፎ ቢገኝ አግባብ ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

__ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጎች__

ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በደንቡ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

__ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ__

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር

e) the batch and lot number of the package; and

f) a description that the salt shall be kept in a cool, clean and dry place.

7. __Inspection__

1/ Any inspector may inspect any processing, storage, transporting or sales premises to ascertain that salt intended for human consumption is iodized.

2/ The inspector while performing his duties shall have the powers provided under sub-article (2) of Article 5 of the Proclamation.

8. __Non-Iodized Salt__

The Authority may, in consultation with the appropriate bodies, issue directives on the processing, importation, storage, distribution, sale and usages of non-iodized salt intended for industrial purpose, and monitor the implementation of same.

9. __Obligation to Cooperate__

Any person shall have the obligation to cooperate with the relevant bodies for the implementation of this Regulation.

10. __Power to Issue Directive__

The Authority may issue directives necessary for the proper implementation of this Regulation.

11. __Penalty__

Any person who violates the provisions of this Regulation or directives issued for the implemention of this Regulation shall be punished in accordance with the relevant provisions of the Proclamation.

12. __Inapplicable laws__

No Regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Regulation, be applicable with respect of matters provided for in this Regulation.

13. __Effective Date__

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 25th day of March 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA